## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# ብሔራዊ የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ኢመቴክ) ፖሊሲና ስትራቴጂ

**አዲስ አበባ**

**መስከረም 2010**

## ማውጫ


የቃላት ፍቺ.......................................................................................i

አህጽሮተ ቃላትና አጫጭር ስያሜዎች...........................................................iii

ምዕራፍ አንድ........................................................................................1

ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ግቦች እና መርሆዎች ..................................................1

1.1 መግቢያ .............................................................................................1
1.2 ብሔራዊ ራዕይ.......................................................................................3
1.3 የኢመቴክ ራዕይ ....................................................................................3
1.4 ተልዕኮ ...............................................................................................3
1.5 ዓላማ .................................................................................................3
1.6 አጠቃላይ ግቦች.......................................................................................3
1.7 መርሆዎች ...........................................................................................4

ምዕራፍ ሁለት .......................................................................................5

የኢመቴክ የትኩረት መስኮች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ..........................................5

2.1 መግቢያ ..............................................................................................5
2.2 የኢመቴክ የፖሊሲ መሰረት ........................................................................5
2.3 የኢመቴክ ፖሊሲ ትኩረት...........................................................................6
2.4 የኢመቴክ መሠረተ ልማት ማሟላት.................................................................7
2.5 የሰው ኃይል ልማት ማሳደግ .......................................................................9
2.6 የኢመቴክ ሕጋዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ዝርጋታና ደህንነት ማረጋገጥ.............................11
2.7 የኢንተርኔት አስተዳደር ሥርዓት ማበጀት.........................................................15
2.8 ኢመቴክ ለመንግሥት አስተዳደር እና አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት .........................18
2.9 የኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ ..............................................................26
2.10 የኮምፒዩተር እና ተያያዥ አገልግሎቶች ልማት ማሳደግ .........................................28
2.11 የኢመቴክ የሥራ ሀሳብ እና ፈጠራን ማበረታታት ...............................................30
2.12 ኢመቴክ ለወጣቶች እና ለሴቶች......................................................................31
2.13 የኢመቴክ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግርን መደገፍ ................................................33

ምዕራፍ ሦስት.......................................................................................35

የፖሊሲው የአፈጻጸም ማዕቀፍ .....................................................................35

3.1 አጠቃላይ ምልከታ .................................................................................35
3.2 የተቋማት አወቃቀር..................................................................................36
3.3 ክትትልና ግምገማ ...................................................................................37
3.4 የወደፊት አቅጣጫ፣ ብሔራዊ የኢመቴክ መሪ ዕቅድ ...........................................38

## የቃላት ፍቺ

| | |
|---|---|
| 1/ የግብርና ኔት | ማለት በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኙ የግብርና ምርምር ጣቢያዎችን የሚያገናኝና እንደ ኢንተርኔት፣ ቪዲዮ-ኮንፈረንስ…ወዘተ፣ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን የሚሰጥ የመረጃ መረብ ነው፤ |
| 2/ ብሮድካስቲንግ | ማለት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንፎርሜሽን መረብ እና በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ቴክኖሎጂዎች የሚደረግ የመረጃ ሥርጭት ነው፤ |
| 3/ ዲጂታል ዲቫይድ | ማለት በአደጉትና ባላደጉት አገሮች ወይም ክልሎች መካከል ያለውን የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ሥርፀት ክፍተት አመላካች ነው፤ |
| 4/ የኤሌክትሮኒክ ንግድ | ማለት እንደ ኢንተርኔት ያሉ የኮምፒዩተር መረቦችን ለንግድ ሥራ በመጠቀም ሸማቾች፣ አምራቾች፣ አቅራቢዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች እና አገናኞች፣ የሚያደርጓቸው የሸቀጥና የንግድ ኢንፎርሜሽን ልውውጥና ተግባራትን ያጠቃልላል፤ |
| 5/ ኤሌክትሮኒክ መንግሥት አስተዳደር | ማለት በመንግሥት የሚሰጡ አገልግሎቶችን የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማቅረብ ሲሆን በመንግሥት ከተገልጋዮች፣ ከንግዱ ማሕበረሰብ እና ከመንግሥት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይጨምራል፤ |
| 6/ የኢትዮጵያ የትምህርት ምርምር ኔትወርክ | ማለት በሀገር ውስጥ ያሉ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል የምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለመጋራት እና ከአለም አቀፋዊ የምርምር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ፈጠራን ለማበረታታት እና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የሚያገለግል የኢንፎርሜሽን መረብ ነው፤ |
| 7/ ኢንፎርሜሽን መሠረት ያደረገ ኢኮኖሚ | ማለት የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ የአንድ አገር ኢኮኖሚ መሰረት መሆን መቻሉን የሚያመለክት ነው፤ |
| 8/ የኢንፎርሜሽን ማህበረሰብ | ማለት የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም የዕለታዊ ህይወቱ አካል ያደረገ ማህበረሰብ ነው፤ |
| 9/ ኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ | ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የብሮድካስቲንግ ቴክኖሎጂዎችና የኢንፎርሜሽን አገልግሎቶች ግንኙነት ጥምረት ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 10/የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ ፓርክ | ማለት የሀገር ውስጥና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የተዘጋጀ ከፍተኛ የኢመቴክ የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ዞን ነው፤ |
| 11/ የኢንኩቤተር ፕሮጀክት/ የኢንኩቤሽን ማዕከል | ማለት መነሻ የካፒታል ኢንቨስትመንት በማቅረብ እና አስፈላጊውን የሥራ አመራር እና የምክር አገልግሎት በመስጠት ጀማሪ የኢመቴክ ፕሮጀክቶች የሚፈልቁበት እና እራሳቸውን ወደቻሉ ተቋማት የሚያድጉበት ማዕከል ነው፤ |
| 12/ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | ማለት ኮምፒዩተሮችን እና የቢሮ ሥርዓት ቴክኖሎጂዎችን ለኢንፎርሜሽን አሰባሰብ፣ አያያዝና አሠረጫጨት መጠቀምን ያጠቃልላል፤ |
| 13/ ኢንተርኔት | ማለት የኢንፎርሜሽን ልውውጥ አገልግሎት የሚሰጡ ዓለም አቀፍ የኮምፒተሮች መረብ ነው፤ |
| 14/ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ | ማለት የኢንፎርሜሽንና መገኛና ቴክኖሎጂን በስፋት በመጠቀም በዳበረ የህብረተሰብ እውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ነው፤ |
| 15/ ስኩል ኔት | ማለት በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን የሚያገናኝና በብሮድካስቲንግ ዘዴ የርቀት ትምህርት የሚሰራጭበት እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎቶች የሚሰጡበት የኢንፎርሜሽን መረብ ነው፤ |
| 16/ ወረዳ ኔት | ማለት የፌደራል፣ የክልልና የወረዳ የአስተዳደር አካላትን የሚያገናኝና የቪዲዮ-ኮንፈረንስ፣ የኢንተርኔት፣ የመልዕክት ልውውጥ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን አገልግሎቶች የሚሰጥ የመንግሥት የኢንፎርሜሽን መረብ ነው፤ |
| 17/ ዩኒኮድ | በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የጽሑፍ ፊደላትን ለመወከል የሚያስችል ወጥና የኢመቴክ ኢንዱስትሪ ስታንዳርድ የሆነ የኮምፒውተር ጽሑፍ ሥርዓት ነው፤ |

**አህጽሮተ ቃላትና አጫጭር ስያሜዎች**

1/ መኢቴሚ - መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

2/ ኢመቴክ - ኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ

3/ ብኢመቴክም - ብሔራዊ የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ ምክር ቤት

# ብሔራዊ የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ኢመቴክ) ፖሊሲና ስትራቴጂ
## ምዕራፍ አንድ
## ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ግቦች እና መርሆዎች

### 1.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኢመቴክ ዕድገትን ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች አንዱ በማድረግ ወስዷል፡፡ ይህም ኢመቴክ የአገሪቱን ግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ እና የኢንፎርሜሽን ተጠቃሚ ማሕበረሰብ በማሸጋገር አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ በእጅጉ የሚያግዝ ቁልፍ አንቀሳቃሽ ኃይል እና አስቻይ መሆኑ ስለታመነ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢመቴክ ከፍተኛ እድገት እያሳየ ይገኛል፡፡ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት እና በመደበው ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ዘመናዊ የሞባይል ኔትወርክ፣ የመደበኛ እና የብሮድባንድ ኢንተርኔት መሠረተልማት በመዘርጋት እና አገልግሎቱን በማስፋፋት ረገድ በመላ አገሪቱ ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በቴሌኮሙኒኬሽን እና በኢመቴክ አገልግሎቶች አቅርቦት ደረጃም በአገሪቱ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የአገራችን የኢመቴክ አጠቃቀም ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ አቻ አገራት ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ዋና ዋና መገለጫዎቹም፣

ሀ) የሕግና የቁጥጥር ሥርዓት አለመሟላት፤

ለ) የመደበኛ ቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት ውስንነት እና የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆን፤

ሐ) የተደራጀ ዳታ እና የኢንፎርሜሽን አቅርቦት ማነስ እና ያሉትም ቢሆኑ ተደራሽ አለመሆን፤

መ) ብቃት ያለው የሰው ኃይል እጥረትና ስለኢመቴክ ጥቅምና ሚና በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ ማነስ፣ እና

ሠ) የግሉ ዘርፍ ያለማደግ

ናቸው፡፡

ለዘርፉ የተሰጠውን አመራር እና ቁርጠኝነት እንዲሁም ኢንቬስትመንት በማሻሻል ረገድ የተጠቀሱት ችግሮች ለመንግሥት ፈታኝ ሁኔታ የመፍጠራቸውን ያህል በሌላ በኩል በአገሪቱ ፈጣን የኢመቴክ ልማትን ለማምጣት ዕድል የሚከፍቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም መንግሥት የኢመቴክ ልማት አስፈላጊነት በመገንዘብ ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርጿል፡፡

የኢመቴክ ፖሊሲ አድማስ ዕውቀትና ኢንፎርሜሽን እንደልማት መሣሪያ እንዲሁም ኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂን እንደ ዘርፍ ወይም ኢንዱስትሪ እስከመሸፈን ይደርሳል፡፡ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ በተጨማሪ ኢመቴክ በአገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ላለው የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ሂደትም ያግዛል፡፡ ዋና ዋና የኢመቴክ የትግበራ መስኮች በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዙሪያ እንደ ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ እና ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ወ.ዘ.ተ. ያጠቃልላል፡፡ ኢመቴክ ዜጎች እንደፍላጎታቸው በፖለቲካዊ ሂደት እንዲሳተፉ፣ እንደዚሁም ከዓለም አቀፍ ዕውቀትና የኢንፎርሜሽን ፍሰት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዕድል በመፍጠር ዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲጠናከር ይረዳል፡፡ በዚህ ረገድ የመንግሥት ዋና ዓላማ ዜጎች ለመንግሥታዊ አገልግሎቶች እንዲሁም ለዕውቀትና ለኢንፎርሜሽን እኩልና ፍትሐዊ ተደራሽነት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም መንግሥት የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ እንዲሁም የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱን ለማጠናከር የኢመቴክን ልማት የማቀላጠፍ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢመቴክ አስራ ሰባቱን የተባበሩት መንግስታት የዘላቂ ልማት ግቦች ለማሳካት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ከልማት ግቦቹ በተለይ በግብ ዘጠኝ እና ኢላማዎቹ የቴክኖሎጂው ዕድገት እና የዲጂታል ዲቫይድ መጥበብ ለኢኮኖሚ ዕድገት እና አካባቢያዊ ተግዳሮቶች ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተመልክቷል፡ ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ውስጥ ኢመቴክ የሚዳብርበት የፖሊሲ መመሪያዎችንና ለዕድገቱ ወሳኝ የሆኑ የስትራቴጂ ጉዳዮችን ይዟል፡፡

ሰነዱ በሦስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ምዕራፍ አንድ ኢመቴክ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለበት ሁኔታና መንግሥት በኢመቴክ አጠቃቀምና አተገባበር ላይ ያለውን ጽኑ ፍላጎት

ይገልፃል። በተጨማሪም የፖሊሲው መሠረታዊ መርሆዎች ከኢመቴክ ራዕይ፣ ተልእኮ፣ ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች አንፃር ይዘረዝራል። ምዕራፍ ሁለት የኢመቴክ ፖሊሲ መሰረቶችን ማለትም የኢመቴክ መሠረተ ልማትን፣ የኢመቴክ ሰው ኃይል ልማትን፣ የኢመቴክ ሕጋዊ ሥርዓትና ደህንነትን እና የፖሊሲውን የትኩረት መስኮች የሚያጠቃልል ነው። በመጨረሻው ምዕራፍ ተቋማዊ ማዕቀፍን የመፍጠር፣ የማቀናጀት፣ የመቆጣጠርና የመገምገም ሥራዎችን ያካትታል።

## 1.2 ብሔራዊ ራዕይ

በሕዝቦች ተሳትፎና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሠባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ሆና ማየት።

## 1.3 የኢመቴክ ራዕይ

የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኑሮና አጠቃላይ ህይወት በኢመቴክ ተጠቃሚ ሆኖ ማየት።

## 1.4 ተልዕኮ

ኢመቴክን በማልማትና በሁሉም ሥፍራ በስፋት በመጠቀም የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻልና ኢመቴክ ለአገሪቱ ዕድገት የሚሰጠውን ድጋፍ ማሳደግ።

## 1.5 ዓላማ

የኢመቴክ ዘርፍን በማሳደግና በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን አስተዋፅዖ በማጎልበት ሀገሪቱ የፈጣን ልማትና ዕድገት ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ።

## 1.6 አጠቃላይ ግቦች

የኢመቴክ ፖሊሲና ስትራቴጂ አጠቃላይ ግቦች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማት ግንባታ በመላ ሃገሪቱ ተደራሽና ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤

ለ/ ኢመቴክን በአግባቡ ለማልማትና ለመጠቀም የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃብት ማፍራትና የህብረተሰቡን የኢመቴክ መሠረታዊ ዕውቀትና አጠቃቀም ማሳደግ፤

ሐ/ ኢመቴክን አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ የሕግ ማእቀፍ እንዲኖርና እንዲሁም ቴክኖሎጂውን በመጠቀም የሚፈጸሙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል አግባብ ያላቸውን የደህንነት ሥርዓቶችና ደረጃዎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፤

መ/ የኢመቴክ አጠቃቀምን በማሳደግ የመንግሥትና የሕዝብ አገልግሎቶችን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ ሙስናን መከላከልና የሀብት ብክነትን መቀነስ፤

ሠ/ ኢመቴክን በመጠቀም የኢኮኖሚውን ምርታማነትንና ብቃትን ማሳደግ፣

ረ/ ከአየር ንብረት ለውጥ እና በአስቸኳይ ጊዜ ከሚደረግ ግንኙነቶች ጋር በተያያዘ ኢመቴክን በመጠቀም የኢንፎርሜሽን ልውውጥን ቀልጣፋ ማድረግ፤

ሰ/ የኢመቴክ ዘርፍን ለማሳደግ የሚያስችል የብሮድባንድ እና የኢመቴክ ኢንዱስትሪን ማጐልበት፤

ሸ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማትንና አገልግሎቶችን በተፈለገው ጥራትና ተዓማኒነት ለሕዝብ ማዳረስ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት እና አገልግሎቶችን በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ ማቅረብ፤

ቀ/ አገራዊ ይዘት ያላቸው የኢመቴክ ልማቶች እና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤

በ/ የኢመቴክን ፈጣን ዕድገት ለማረጋገጥ የግሉ ዘርፍ ድርሻ በሂደት ማስፋፋትና ማጠናከር።

## 1.7 መርሆዎች

የኢመቴክ ፖሊሲና ስትራቴጂ አፈፃፀም የሚመራው በሚከተሉት መርሆዎች መሠረት ይሆናል፤

ሀ/ ለፖሊሲው የተሳካ አፈፃፀም መንግሥት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ስትራቴጂያዊ አመራር ይሰጣል፤

ለ/ የፖሊሲው ዓላማዎችና ግቦች የአገሪቱን አጠቃላይ የልማት ግቦችና ፕሮግራሞች ለመደገፍና ለማጠናከር ይሆናል፤

ሐ/ በአገሪቱ ኢመቴክንና ሌሎች መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን የማስፋፋት ሥራ የኢመቴክን ፍትሐዊ ስርጭትና ለሁሉም ማዳረስ (universal access) የሚለውን መርህ በሚያጠናክር መልኩ ይሆናል፤

መ/ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶችና ወጣቶች ኢመቴክን ያለምንም ችግር መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥና ኢመቴክን ለመጠቀም የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ፤

ሠ/ በሀገሪቱ የኢመቴክን ልማት በተመለከተ ከግሉ ዘርፍ፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከልማት ድርጅቶች፣ ከህብረተሰቡ ጋር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ማበረታታትና መደገፍ ብሎም አህጉራዊና አለማቀፋዊ ትብብር መፍጠርና ማጠናከር፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የኢመቴክ የትኩረት መስኮች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

### 2.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኢመቴክ ፖሊሲ የአገሪቱ አጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎችና ግቦች አንዱ መሠረታዊ አካል ነው፡፡ በመሆኑም ፖሊሲው ትኩረት የሚያደርገው ለአገሪቱ የኢመቴክ ልማት መሳካት ስትራቴጂያዊ ፋይዳ ይኖራቸዋል ተብለው በሚታሰቡትና ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የፖሊሲ መሰረቶች፣ ስትራቴጂዎችና የትኩረት መስኮች ላይ ይሆናል፡፡

### 2.2 የኢመቴክ የፖሊሲ መሰረት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ኢመቴክ ፖሊሲ የአገሪቱን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዓላማ እና ግብ ለማሳካት ወሳኝ ከሆኑት መሠረቶች አንዱ ነው፡፡ ፖሊሲውን በአጠቃላይ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የሚከተሉት አራት ወሳኝ ጉዳዮች መሟላት አለባቸው፤

ሀ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማት ዕድገት፤

ለ/ የሰው ኃይል ልማት፤

ሐ/ የኢመቴክ ሕጋዊ ሥርዓትና ደህንነት፣

መ/ የኢንተርኔት አስተዳደር ሥርዓት ማበጀት።

## 2.3 የኢመቴክ ፖሊሲ ትኩረት

የፖሊሲው መሰረቶች አንዴ ከተጣሉ በኋላ በአገሪቱ ውስጥ የኢመቴክ ሀብትን ለመጠቀም የሚያስችል የተሻለ ሁኔታ የሚፈጠር ሲሆን ከኢመቴክ ጋር የተገናኙ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና ኢመቴክን በመላ አገሪቱ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል። የሚከተሉት ቁልፍ ዘርፎች፣ ኢንዱስትሪዎች እና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የኢመቴክ ፖሊሲ ዋና ክፍሎች ሲሆኑ የአገሪቱን ኢኮኖሚ እና ማሕበረሰብ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚለውጡ ይታመናል።

ሀ/ የኢመቴክን ለመንግሥት አስተዳደር /ኤ-መንግሥት/ መጠቀም፣ በተለይ ኢመቴክን ለትምህርት ዘርፍ፣ ለተሻለ ጤና አገልግሎት እና ለዘመናዊ ግብርና ልማት መጠቀም፤

ለ/ የኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት፤


ሐ/ ኢመቴክ ለምርምርና ልማት፤

መ/ ኮምፒዩተር እና ተያያዥ አገልግሎቶች፤

ሠ/ የሥራ ሀሳብ እና ፈጠራ፤

ረ/ ወጣቶች እና ሴቶች።

ከላይ የተጠቀሱትን የኢመቴክ የፖሊሲ መሰረቶች እና የትኩረት አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በየዘርፉ የተቀየሱት ዓላማዎችና ግቦች እንዲሁም ስትራቴጂዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።




## 2.4 የኢመቴክ መሠረተ ልማት ማሟላት

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

*ሀገራችን ኢትዮጵያ የኢመቴክ ልማትን በሁሉም ቦታ ለማዳረስ ወሳኝ ድርሻ ያላቸውን የሃይል አቅርቦትና የመገናኛ ኔትወርክ የመሳሰሉ የተቀናጁ መሰረተ ልማቶችን በቅድሚያ ማሟላት ይጠበቅባታል:: ኢመቴክ የሚሰጠውን ጥቅም በሚገባ ለማግኘት አገሪቱ ዘመናዊ እና ብቃት ያላቸው መሠረተ ልማቶች ሊኖሯት ይገባል::*

*በመሆኑም የኢመቴክንና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን አቀናጅቶ የማሳደግ ዓላማን ከግብ ለማድረስ እንዲቻል መንግሥት አግባብ ያላቸውን ስትራቴጂዎች በመጠቀም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ለማሳካት ጥረት ያደርጋል::*

## 2/ ዓላማ

የኢመቴክ አገልግሎቶችን ለማልማትና ህብረተሰቡን በስፋት ተጠቃሚ ለማድረግ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የብሮድባንድና ሌሎች የመገናኛ መሠረተ ልማቶችን በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች መዘርጋት፡፡

## 3/ ግቦች

የኢመቴክ መሠረተ ልማት ማዳረስ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ እውቀትና ኢንፎርሜሽን ለዜጎች ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በጥራትና በስፋት እንዲዳረስ የአገሪቱን የመገናኛ እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረት ልማትና አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ዘመናዊ ማድረግ፤

ለ/ ቁልፍ ለሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ፍላጎት የሚያሟላና የመንግሥት አገልግሎትን ለማቅረብ የሚያስችል የተቀናጀ የመልቲሚዲያ አገልግሎት እንዲሁም ያልተማከለ የዳታ ማከማቻና አገልግሎት የሚውል ከፍተኛ ትራፊክ የማስተላለፍ አቅም ያለው የመገናኛ አውታርን የሚያጠቃልል የኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት መዘርጋት፤

ሐ/ ብሔራዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ፤

መ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማትና ሥርዓቶች አጥጋቢ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውንና ውጤታማ እና ጥራት ባለው ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ መሠረተ ልማትን ለማዳረስ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማት በተለይም የብሮድባንድ ልማት የሚመራበት መሪ እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር፤

ለ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማት፣ አውታሮችን እና አገልግሎቶችን ማልማት፣ ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ሐ/ በብሔራዊና በክልል ደረጃ ከፍተኛ ፍጥነት ያላቸው የመገናኛ አውታሮች መዘርጋት፤

መ/ የኢመቴክ አገልግሎቶችን ለተጠቃሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፤

ሠ/ የኢመቴክ መሠረተ ልማት ዕድገትን በሚደግፍ መልኩ የብሔራዊ የኤሌክትሪክ ማስተላለፍያ አውታርን (National Grid) ዘመናዊ ማድረግ እና ማስፋፋት፤

ረ/ ለኢመቴክ መሣርያዎችና አገልግሎት የሚውል አዋጭና ወጪ ቆጣቢ የሆነ አማራጭ የታዳሽ ኃይል ምንጭ ማፈላለግና ማልማት።

## 2.5 የሰው ኃይል ልማት ማሳደግ

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

መንግሥት የኢመቴክ ትምህርትና ሥልጠናን በሁለተኛና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ በማድረግ ሂደት ላይ ይገኛል። ዓላማውም የ መሠረታዊ ዕውቀትን ለማስጨበጥና ብሎም በአገሪቱ የኢመቴክ ባለሙያዎች የሚፈጠሩበትን መሠረተ ለመጣል ነው።

የኢመቴክ ልማት ዘርፍ እየተጠናከረ በሚሄድበት ወቅት የኢመቴክ ባለሙያ ፍላጎትም በዚያው ልክ እያደገ እንደሚሔድ ይታሰባል። ከዚህ በተጨማሪ ህብረተሰቡን የኢመቴክ ተጠቃሚ ለማድረግ የኮምፒተርና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ መሠረታዊ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው።

በመሆኑም የኢመቴክ ፖሊሲ በኢመቴክ የሰው ኃይል ልማት ዙሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ለማሳካት ትኩረት ያደርጋል።

### 2/ ዓላማ

አገሪቱ ኢመቴክ ለማልማትና ለመጠቀም የሚያስችላት በየደረጃው የኢመቴክ ዕውቀትና ክህሎት የጨበጠ የሰው ኃይል ማፍራት።

### 3/ ግቦች

የኢመቴክ የሰው ኃይል ልማት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ የኢመቴክ ትምህርትና ሥልጠናን የሚሰጡ የመንግሥትና የግል ተቋማትን አቅም ማጠናከር፤

ለ/ የሰለጠነ የኢመቴክ ባለሙያ አቅርቦትን ማሳደግ፤

ሐ/ በሕብረተሰቡ ውስጥ መሠረታዊ የኢመቴክ ዕውቀት እንዲዳብር ማድረግ፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ የሰው ኃይል ልማትን ለማሳደግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የኢመቴክ የሰው ኃይል ልማት ዕቅዶች ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፤

ለ/ አሁን ያለውን የባለሙያ እጥረት ለመቅረፍና ወደፊት በሚኖረው ዕድገት ምክንያት የሚጠበቀውን የኢመቴክ ባለሙያ ፍላጎት የሙያ ስብጥርን ባካተተ መልኩ ጭምር ለማሟላት የኢመቴክ ሙያ ልማትን በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ማስፋፋት፤

ሐ/ የኢመቴክ ሥልጠና አሠጣጥን ለማጠናከርና የቴክኖሎጂ ፈጠራን ለማበረታታትና ለማስተዋወቅ እንዲችሉ የግሉን ዘርፍ በትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪ አደረጃጀት መደገፍና ማበረታታት፤

መ/ ለአገሪቱ ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚያስፈልገውን የኢመቴክ የሰው ኃይል ፍላጎት በመለየት ልዩ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ ተፈላጊውን የሰው ኃይል በፍጥነት ማሳደግ፤

ሠ/ ኤሌክትሮኒክስ ምህንድስናና ሌሎች ከኢመቴክ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የትምህርት መስኮች በአዲስ መልክ በማደራጀትና አዳዲስ የኢመቴክ ለውጦች እና እድገቶችን ባቀፈ መልኩ የኢንዳስትሪውን የሰው ኃይል ፍላጐት እንዲያሟሉ ማድረግ፤

ረ/ የባለሙያዎች የሥራ ፈጠራና የሥራ እርካታ እንዲኖር ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍልሰትን መቀነስ፤

ሰ/ የኮምፒውተር ትምህርትና ሥልጠና በህብረተሰቡ ዘንድ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## 2.6 የኢመቴክ ሕጋዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ዝርጋታና ደህንነት ማረጋገጥ

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

የኢመቴክ አጠቃቀም እና ሁለንተናዊ አተገባበር ተስማሚ የሕግ ሥርዓት የሰፈነበት አካባቢን ይፈልጋል፡፡ ይህ ሁኔታ ኢመቴክን እንደ አንድ ዘርፍ ወይም ኢንዱስትሪ ለማሳደግም ሆነ ኢመቴክን እንደ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሣሪያ መጠቀምን ይመለከታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ያለው የኢመቴክ የሕግ ሥርዓት ማዕቀፍ በፍጥነት በማደግ ላይ ከሚገኘው ብሔራዊ እና ዓለምአፋዊ የኢመቴክ ዘርፍ ፈታኝ ሁኔታዎች ጋር አብሮ ሊሄድ የማይችል መሆኑን መንግሥት ይገነዘባል፡፡

በተጨማሪም በአገሪቱ ውስጥ የተጀመረው የኢመቴክ ልማት ባልተቀናጀ ሁኔታ ሲካሄድ በመቆየቱ የተለያዩ ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን የተከተሉ ግዥዎችና ትግበራዎች እንዲኖሩ በማድረግ አላስፈላጊ የሥራ ድግግሞሽና የሀብት ብክነት እያስከተለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ መንግሥት ይህን በመገንዘብ ልማቱ አግባብ ባላቸው ደረጃዎችና ምርጥ ተሞክሮዎች መመራት እንዳለበት ያምናል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ የኮምፒዩተሮችና የኢንተርኔት አጠቃቀም ተገቢ ጥንቃቄና ጥበቃ ካልተደረገለት የተለያዩ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ የመረጃዎች መጥፋት፣ የመረጃ መዛባት፣ በተጠቃሚዎች፣ በግለሰቦች፣ በንግድ ሥራዎችና በመንግሥት ድርጅቶች ጭምር የደህንነት ሥጋቶችና ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም አስፈላጊ የጥራት ደረጃዎችን በሥራ ላይ ማዋልና እና በሕግ የሚመራ ኢመቴክን በስፋት መጠቀምና ተግባራዊ ማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የመረጃ ደህንነትና ደረጃዎች የኢመቴክ ልማት ሂደት አካል እንደመሆናቸው መንግሥት ደህንነቱ የተጠበቀ የኢመቴክ አካባቢና አግባብ ያላቸው ደረጃዎች መኖር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ስለሆነም መንግሥት ኢመቴክን ለመምራትና ትግበራውን ለማመቻቸት የሚከተሉትን የሕግ ሥርዓትና የደህንነት ማዕቀፍ አካል የሆኑትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 2/ ዓላማ

ብሔራዊ፣ ተቋማዊ እና ግለሰባዊ ደህንነትን በማስጠበቅ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ጥመርታን መሠረት በማድረግ ተቋማዊ የሕግና የቁጥጥር ሥርዓቶችን በማስፈን አገራዊ የኢመቴክ ልማትን መደገፍ።

## 3/ የኢመቴክ የሕግ ሥርዓት ማዕቀፍ ዝርጋታ ግቦችና ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ የሕግ ሥርዓት ዝርጋታ የሚከተሉት ግቦችና ስትራቴጂዎች ይኖሩታል፤

### ግቦች

ሀ/ በመላው አገሪቱ ኢመቴክን በሚገባ ለመጠቀምና ለማስፋፋት እንዲቻል በፌደራልና በክልል ደረጃ ተጣጥመው የሚሄዱ ደረጃዎችንና መመሪያዎችን ማውጣት፤

ለ/ የአእምሮአዊ ንብረት መብት ጥበቃን በኢመቴክ ውስጥ ማረጋገጥ፤

ሐ/ የኢመቴክ ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና የቁጥጥር ሥርዓቶች ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎቶችና አቅም ግንባታን የሚያካትቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

መ/ ምቹ የሕግና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ለኢመቴክ ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ማበረታታት፣

ሠ/ የኤሌክትሮኒክስ ተረፈ ምርት አስተዳደር ለመተግበር እና ምቹ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል የሕግና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ።

### ስትራቴጂዎች

ሀ/ አግባብነት ያለው የሕግና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ሥራ ላይ ማዋል፤

ለ/ የኢንፎርሜሽን ሀብቶችና አገልግሎቶችን ከማልማት ጋር የተያያዙ የሕግ ማዕቀፎችን ማውጣትና በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ በተቀናጀ ሁኔታ እንዲካተቱ ማድረግ፤

ሐ/ በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎችና ሕጎች በመከለስና በማሻሻል ኢመቴክ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት፤

መ/ ለኢመቴክ ልማት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ፖሊሲዎችና ሕጎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ መለየትና ማስወገድ፤

ሠ/ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ ላይ የተመሠረተ የማህደር አያያዝና አደረጃጀት፣ አቀራረብ፣ አጠቃቀም እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸው ኢንፎርሜሽን አወጋገድ ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ፤

ረ/ የኢመቴክ ልማት የሚደግፉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የሚያበረታቱ ምቹ የህግና የቁጥጥር ሥርዓቶችን መፍጠር፤

ሰ/ የፈቃድ አሠጣጥ መስፈርቶች እና አሰራሮችን በመከለስና በማሻሻል በተለይ በገጠር አካባቢዎች የተለያዩ የኢመቴክ አገልግሎቶች ተደራሽነት መኖሩን ማረጋገጥ፣

ሸ/ ከአገራዊና ዓለም አቀፋዊ የኢመቴክ እድገቶች ጋር አብሮ ለመጓዝ በሚያስችል መልኩ የሕግና የቁጥጥር ማዕቀፎችን በየጊዜው መከለስ፤

ቀ/ ከኢመቴክ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ለማህበረሰቡ ጠንቅ የሆኑ ድርጊቶችን ለመከላከል እንዲቻል የቁጥጥር ሥርዓት ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፤

በ/ የኢመቴክ ምርቶችን ከማቅረብና አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ የጥራት ቁጥጥርና የሥራ አመራር መመሪያዎችና ደረጃዎችን በሥራ ላይ ማዋል፤

ተ/ የኤሌክትሮኒክ ተረፈ ምርቶች አያያዝ የሚፈለገውን ደረጃ በተከተለ መልኩ እንዲሆንና ዘርፉ ለከባቢያዊ ሁኔታ ምቹ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት እና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤

ቸ/ የኢንፎርሜሽን መረብ፣ ዳታ እና የኢንፎርሜሽን ስርዓቶችን ከጥቃት እና ካልተፈቀደላቸው አካላት ተደራሽነት በመጠበቅ ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲን ማጠናከር፤

ነ/ የኢመቴክ ሕጐች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ዓለማቀፋዊና አህጉራዊ ደረጃዎችና ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

ኘ/ የኮምፒውተር መረብ የርስ በርስ መገናኘትና መሥራት ደረጃዎችን ማውጣት፤

አ/ የአገራዊ ቋንቋዎች የሆሄያት ሥርዓትና የኪቦርድ አቀማመጥ ማስተዋወቅና ዩኒኮድ (UNICODE) ቴክኖሎጂን መጠቀም፣

## 4/ የኢመቴክ ደህንነት የማረጋገጥ ግቦችና ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ ደህንነትን ማረጋገጥ የሚከተሉት ግቦችና ስትራቴጂዎች ይኖሩታል፤

### ግቦች

ሀ/ የብሔራዊ፣ ተቋማዊ እና ግለሰባዊ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ሥርዓት ጥበቃና ደህንነት ማረጋገጥ፤

ለ/ በኢንፎርሜሽን አጠቃቀም ዙሪያ በህዝቡ ዘንድ ተአማኒነትና መተማመንን ማሳደር እንደዚሁም ጠንካራ የዳታ (ዊሂብ) እና የኢንፎርሜሽን መረብ አስተማማኝነት መጠበቅ፤

ሐ/ እንደ የወሲብ ንግድ፣ ማጭበርበር፣ የተደራጀ ወንጀል እና ሽብር፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር የመሳሰሉ ድንበር ዘለል ወንጀሎች በመከላከል ዙሪያ ለሚደረገው ትግል አስተዋጽኦ ለማበርከት የሳይበር ወንጀል እና አግባብነት የሌለው የኢመቴክ አጠቃቀምን መከላከል፣ መከታተልና የአፀፋ እርምጃ መወሰድ፤

መ/ በኢኮኖሚውና በህብረተሰቡ ውስጥ በተስፋፋው የኢመቴክ ትግበራ ምክንያት በብሔራዊ ደህንነት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን መለየትና በአግባቡ መፍታት፤

ሠ/ በኢመቴክ ፖሊሲ ትግበራ፣ አፈፃፀምና ክትትል ላይ የተሰማሩ መንግሥታዊ አካላትን የማስፈፀም አቅም መገንባትና ወንጀል የመከላከልና የመቆጣጠር አቅምን ማጎልበት፡፡

### ስትራቴጂዎች

ሀ/ ኢትዮጵያ በኢንፎርሜሽን ማህበረሰብ ውስጥ ያልተገደበና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራት ለማመቻቸት የሳይበር-ነክ ተግባራትን መቆጣጠር፣

የአእምሮአዊ ንብረት መብቶችን፣ የዳታ ጥበቃና ደህንነትን፣ የኢንፎርሜሽን ማግኘት ነፃነትን፣ የኮምፒዩተርና የሳይበር ወንጀል እንደዚሁም ሌሎች የሳይበር ሕጐች የሚወጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

ለ/ አግባብነት የሌለው የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን ሥርዓቶችን አጠቃቀም ለመከላከል የሚያስችል ሕግ ማውጣትና መተግበር፤

ሐ/ የግንኙነት መረቦችን፣ የዳታና የኢንፎርሜሽን ሥርዓቶች ከጥቃትና አግባብነት በሌላቸው አካላት እጅ እንዳይገቡ መከላከልና የዜጐችን መብቶች ማስከበር፤

መ/ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትንና ዳታን አለአግባብ በመገልገል፣ በቸልተኝነት ወይም የዳታ አደጋን ቀድሞ መከላከል እና ዳታን መልሶ የማግኘት የአሠራር ሂደትን ያለመከተል ሁኔታዎች ላይ አስፈላጊው የሕግ እርምጃ መወሰዱን ማረጋገጥ፤

ሠ/ የህግ አስፈጻሚ አካላት አግባብ ያለው የኢመቴክ መሠረተ ልማትና አገልግሎቶች እንዲያገኙ ማድረግ፤

ረ/ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ያለውን ተቋማዊና የሰው ኃይል አቅምን በማጠናከር የመገናኛና ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነትን ማረጋገጥ፤

ሰ/ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን መረቡን ከቫይረስና ሕጋዊ ካልሆነ እንቅስቃሴ እንደዚሁም ጣልቃ ገብነት መከላከልና በየጊዜው ቁጥጥር ማድረግ፤

ሸ/ በኢመቴክ ተጠቃሚዎች ዘንድ ስለ ዳታና ኢንፎርሜሽን ደህንነት ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ፤

ቀ/ ከኢመቴክ ደህንነት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከወቅታዊ ምርጥ ተሞክሮዎች ዕድገት ጋር አብሮ መጓዝ።

## 2.7 የኢንተርኔት አስተዳደር ሥርዓት ማበጀት

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

የኢንተርኔት አስተዳደር የኢመቴክ ፖሊሲና ስትራቴጂ ዋነኛ ፈታኝ ሁኔታ ነው። የኢንተርኔት አስተዳደር ዓለምአቀፍ የኢንተርኔት የለውጥ ሂደት እና አጠቃቀም መርሆች፣ ልማዶች፣ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና ፕሮግራሞች

ሥርዓት ማበጀትን ይመለከታል። ኢንተርኔት በዜጎች የዕለት ተዕለት ህይወት ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ እያደገ በመምጣቱ ምክንያት የኢንተርኔት ፖሊሲ ጉዳይ ቀስ በቀስ ከሀገራዊ ጉዳዮች አልፎ ወደ ዲፕሎማሲ እና ሌሎች ዓለምአቀፍ የፖሊሲ ጉዳይነት ተለውጧል። በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንተርኔትን በተመለከተ በቁልፍ የኢንተርኔት ሀብቶች አስተዳደር፣ የማህበራዊ ሚዲያ ቁጥጥር፣ የኢንተርኔት ይዘት አስተዳደር፣ የአእምሮ ንብረት፣ የግለሰብ ነፃነት፣ የህግ አፈፃፀምና የሳይበር ደህንንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተፅእኖ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት የኢንተርኔት አስተዳደር ጉዳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የፖሊሲ ጉዳይ ቢሆንም መንግስት በሌሎች ዓለምአቀፍ የህዝብ ፖሊሲዎች ላይ በሚያደርገው የተሳትፎ ደረጃ ሚናውን እየተጫወተ አይደለም። በሀገራችን ግልጽ የሆነ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የኢንተርኔት አስተዳደር አቅጣጫ አለመኖር መንግስት በጠቅላላው ኢመቴክን፣ በተለይ ደግሞ ኢንተርኔትን በማስፋፋት እና በመቆጣጠር ረገድ የሚያደርገውን ጥረት ይበልጥ ሊያወሳስብ ይችላል።

በመሆኑም መንግሥት የኢንተርኔት አስተዳደር ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው የኢመቴክ ፖሊሲና ስትራቴጂ አካል መሆን እንዳለበት በማመን የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

### 2/ ዓላማ

ዓለም አቀፋዊ የኢንተርኔት አስተዳደር የአገሪቱን እና የዜጎች ፍላጎት የሚያስጠብቅ እንዲሆን ማድረግ።

### 3/ ግቦች

የኢንተርኔት አስተዳደር ሥርዓት ማበጀት የሚከተሉት ግቦችና ስትራቴጂዎች ይኖሩታል፤

ሀ/ ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፤

ለ/ የኢንተርኔት አስተዳደር ፖሊሲ ውሳኔዎች በሀገራት እኩል ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፤

ሐ/ የዓለም አቀፍ ኢንተርኔት አስተዳደር አሠራር፣ ሂደቶችና ውሳኔዎች በዲሞክራሲያዊ መንገድና በግልጽነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ መስራት፤

መ/ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚና ግልጽ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኢንተርኔት አስተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ ከልማታዊ መንግሥት መርሆች ጋር የተጣጣመና የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም መሠረት ያደረገ ብሔራዊ የኢንተርኔት አስተዳደር ስትራቴጂ መዘርጋት፤

ለ/ የኢንተርኔት አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለተመለከቱ ፖሊሲ ጉዳዮች ምንጭ በመሆን የሚያገለግል ብሔራዊ የኢንተርኔት አስተዳደር ፎረም እንዲኖር ማድረግ፤

ሐ/ በፖሊሲ አውጭዎች እና በሕብረተሰቡ ዘንድ በኢንተርኔት አስተዳደር ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤

መ/ መንግስታዊ ያልሆኑ እንደ ሙያ ማሕበራት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማህበረሰብ፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ምሁራን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች እና ግለሰቦችን ሀገራዊ በሆነ የኢንተርኔት አስተዳደር ዙሪያ የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግና ማበረታታ፤

ሠ/ መንግሥት ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ክልላዊ በሆኑ የኢንተርኔት አስተዳደር መድረኮች ላይ በመሳተፍ በዓለም አቀፍ የኢንተርኔት ፖሊሲ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ዋና ተዋናይ እንዲሆን ማድረግ፤

ረ/ ብሔራዊ ጥቅሞችን በማስቀደም፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ በመመስረት በዓለም አቀፋዊና በአህጉራዊ መድረኮች መሳተፍና ምርጥ ተሞክሮዎችና አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣

ሰ/ የኢንተርኔት አስተዳደርን የአገሪቱ የኢመቴክ ልማት አጀንዳ ማድረግ፡፡

## 2.8 ኢመቴክ ለመንግሥት አስተዳደር እና አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

በማስፈጸም የአቅም ግንባታ ሥራዎች የመንግሥት አገልግሎቶች አቅርቦት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የተለያዩ እርምጃዎች ከመውሰድ ጐን ለጐን ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ የአሠራር ሂደቶችና የሥርዓት ማሻሻያዎች እንደዚሁም የአመለካከትና የባህሪ ለውጦች፣ በአጠቃላይ የዳበሩ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች እንዲጎለብቱ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ መንግሥት ኢመቴክ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር ማስፈን ያለውን ድርሻ በመገንዘቡ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለዕድገቱ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም መንግሥት የኢመቴክ ለመንግሥት አስተዳር ሥርዓትን በመንግሥትና በሕዝብ አገልግሎቶች ውስጥ ለማስፋፋት፣ ለመተግበርና ለማጠናከር የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2/ ዓላማ

የኤሌክትሮኒክ መንግሥት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግና በመጠቀም የሕዝብ አስተዳደር እና አገልግሎት ዘመናዊ በማድረግ ውጤታማና ብቃት ያለው የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ፡፡

### 3/ ግቦች

የኢመቴክ ለመንግሥት አስተዳደር እና አገልግሎት (ኤ-መንግሥት አስተዳደር) ተግባራዊ ማድረግ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ በፌዴራልና በክልል እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ውስጣዊና ውጫዊ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት አቅርቦትና የኢንፎርሜሽን ልውውጥን ለማቀላጠፍ ጠንካራ፣ በቀላሉ ሊሻሻሉ የሚችሉና ከፍ ሊደረጉ የሚችሉ የኢንፎርሜሽንና መገናኛ መሠረተ ልማት መገንባት እና ስራ ላይ ማዋል፤

ለ/ በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራልና ክልላዊ መንግሥታት መዋቅሮች በሙሉ ግንኙነታቸው በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ በስፋት እንዲጠቀሙ በማስቻል

አገልግሎታቸውን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የሥራ ማስኬጃ እና የግዢ ወጪያቸውን መቀነስ፤

ሐ/ የኢንፎርሜሽንና የመንግሥት አገልግሎቶች በቀላሉ የሚገኙበትን መንገድ በማመቻቸት መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደትን ማጠናከር፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ ለመንግሥት አስተዳደር እና አገልግሎት (ኤ-መንግሥት አስተዳደር) ተግባራዊ ማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ መንግሥት ለመንግሥት፣ መንግሥት ለንግዱ ዘርፍ፣ መንግሥት ለዜጎችና መንግሥት ለሠራተኞች በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ያተኮረ አጠቃላይ የኤ-መንግሥት ስትራቴጂ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤

ለ/ የመንግሥትና የሕዝብ አገልጋዮችን የኮምፒዩተር አጠቃቀም ክህሎት ለማሻሻልና ከፍ ለማድረግ የሥራ ላይ ሥልጠና ፕሮግራሞች ማዘጋጀት እና መስጠት፤

ሐ/ በመንግሥት ተቋማት የኢመቴክ ሥርዓቶች፣ ሶፍትዌሮች እና መሣሪያዎች ግዥ፣ ተከላ እና ጥገናን የሚመለከቱ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ማዘጋጀት፤

መ/ ኤ-መንግሥትን ተግባራዊ በማድረግ በኩል የሕግ ጥበቃ ያላቸው፣ ነፃና ኦፕን ሶርስ ሶፍትዌሮች አጠቃቀምን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፤

ሠ/ በመልቲ-ሚዲያ ይዘት ላይ የተመሠረቱ፣ ለብዙሃን ፍጆታ የሚውሉ እና ለኢንፎርሜሽን አቅርቦት የሚውሉ የአፕሊኬሽን ልማት ጥረቶችን መደገፍና ማበረታታት፤

ረ/ በአገራዊ ቋንቋ ላይ የተመሰረቱ የመንግሥት ፖርታሎችን ማልማትና ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላም ክትትል ማድረግ፤

ሰ/ በሞባይል አፕሊኬሽኖች፣ በህዝብ የመኢቴክ ማዕከላት እና በገጠርና በከተማ አካባቢዎች በሚገኙ የኢንፎርሜሽን ኪዮስኮች በመጠቀም

የመንግስት አገልግሎቶችን ለዜጎች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ማቅረብ እና አገልግሎቶቹ በአግባቡ መሰጠታቸውን መከታተል፤

ሸ/ በመላው አገሪቱ ግለሰቦች የኮምፒውተር ባለቤት እንዲሆኑና የኢንተርኔት አገልግሎትን እንዲጠቀሙ ማበረታታት።

### 2.8.1 ኢመቴክን ለትምህርት ዘርፍ ማዋል

#### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

ትምህርትና ሥልጠና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የማዕዘን ድንጋይ መሆኑን መንግሥት ይገነዘባል። በመሆኑም ኢመቴክን በመጠቀም የሰው ሃይል ልማቱን መደገፍና ማፋጠን ያስፈልጋል።

ኢመቴክ የትምህርት ዕድገትን በማቀላጠፍ ግለሰቦችም ሆኑ አገሮች ባለንበት የዕውቀትና የኢንፎርሜሽን ዘመን የሚኖራቸውን ተወዳዳሪነት በማጎልበት ኢንፎርሜሽን እና ዕውቀት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ ይረዳል። አብዛኛው ሕዝብ የሚኖረው በገጠር አካባቢ በመሆኑ የትምህርት ጥራቱንና ተደራሽነቱን ለማሻሻል ኢመቴክ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም መንግሥት የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች በመንደፍ ኢመቴክን ለትምህርት ልማት ለመጠቀም ይሠራል።

#### 2/ ዓላማ

ኢመቴክን በሁሉም ደረጃ በሚሰጡ የትምህርትና የሥልጠና መርሐግብሮች ውስጥ እንደ አንድ ፕሮግራም እንዲካተት ማድረግና በተቻለ መጠን ትምህርትን በሰፊው ለማዳረስ ኢመቴክን በሥራ ላይ ማዋል።

#### 3/ ግቦች

ኢመቴክን ለትምህርት ዘርፍ ማዋል የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ ጥራት ያለው የ ትምህርት እንዲስፋፋና እንዲዳረስ በማድረግ ኢመቴክ የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓት አካል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ ትምህርትን ለሁሉም በማዳረስ መርህ ኢመቴክን የመጠቀም ባህልና ግንዛቤ ማስፋፋትና የኮምፒውተር አጠቃቀም መሠረታዊ እውቀት መዳረሱን ማረጋገጥ፤

ሐ/ በትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆችና በዩንቨርስቲዎች ኢመቴክን ለማስፋፋት እና ለመጠቀም እንዲቻል የምዘና ደረጃዎች እና መመሪያዎችን ማውጣት፤

መ/ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ሥልጠናና ክህሎት እንዲያገኙ በማድረግ ኢመቴክን ለመጠቀም በቂ ዕድል እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ሠ/ ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በስኩል ኔት እና የኢትዮጵያ የትምህርት ምርምር ኔትወርክ በማገናኘት እና የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ የኢመቴክ መሠረታዊ ዕውቀትን በህብረተሰቡ ውስጥ ለማስረፅ የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፉ ማስቻል፤

ረ/ ኢመቴክን በመጠቀም በተለምዶ እየሰሩ የሚገኙ የሕዝብ ቤተመፃህፍትን በዲጂታል የኢንፎርሜሽን መረብ ሥርዓት የተሳሰሩ ቤተመፃህፍትነት መቀየር እና አዳዲስ ዘመናዊ ቤተመፃህፍት ማቋቋም፤

ሰ/ የኤሌክትሮኒክ የርቀት ትምህርትንና ቨርቹዋል የመማር ዘዴን በማዳበር የትምህርትና ስልጠናን ዕድል ማስፋፋት፤

ሸ/ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ኢመቴክ-ነክ በሆኑ የትምህርትና ሥልጠና መርሃ-ግብሮች የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያድግ ማድረግ፤

ቀ/ በሀገሪቱ ውስጥ በኢመቴክ የታገዘ ትምህርትና ሥልጠና እንዲስፋፋ ከግሉ ዘርፍ፣ የሁለትዮሽ ወይም የሶስትዮሽ እና ከዛ በላይ ስምምነት ከሚያደርጉ አገራት እና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር መተባበር።

## 4/ ስትራቴጂዎች

ኢመቴክን ለትምህርት ዘርፍ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የኢመቴክ ትምህርት በኮሌጆችና በዩኒቨርስቲዎች እንዲካተት ሥርዓተ ትምህርቱን ማሻሻል፤

ለ/ መምህራን ሥልጠና እንዲያገኙና የሥራ ሁኔታዎችም እንዲመቻቹላቸው በማድረግ የኮምፒውተር ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው በርካታ የኢመቴክ መምህራንን ማፍራት፤

ሐ/ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ መሰረታዊ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች እና ተያያዥ ቁሳቁሶችን በተመጣጣኝ ዋጋ የማምረት፣ የመጠቀምና በስፋት የማሰራጨት እንቅስቃሴን ማበረታታት፤

መ/ መምህራንና ተማሪዎች የኮምፒውተር ሀርድዌሮችና ሶፍትዌሮችን ጨምሮ የተለያዩ የኢመቴክ ውጤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችሉ ልዩ ልዩ የፋይናንስ ድጋፍ ፓኬጆችንና ሥርዓቶችን ማዘጋጀት፤

ሠ/ በመካሄድ ላይ ያለውን የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ፕሮግራም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎችና በመላው አገሪቱ ማስፋፋት፤

ረ/ ትምህርት ቤቶችን፣ ኮሌጆችን፣ ዩኒቨርስቲዎችንና ቤተመፃህፍቶችን በኤሌክትሮኒክ መረብ በማገናኘትና በማያያዝ ተማሪዎችና መምህራን የዘመናዊ ዕውቀትና ኢንፎርሜሽን ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማስቻል፣

ሰ/ ዲጂታል የትምህርት መሣሪያዎች እንዲዘጋጁ፣ እንዲሰራጩ እና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ማበረታታት፤

ሸ/ ልዩ የኢመቴክ ሥልጠና መርሐ-ግብሮችን ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች በመስጠት የፆታ እና የማህበራዊ ጥቅም አለመመጣጠን ሁኔታዎችን ደረጃ በደረጃ ማስቀረት፤

ቀ/ የመንግስት እና የግል ተቋማት አጋርነትን በማመቻቸትና በማጠናከር የኤሌክትሮኒክ የርቀት ትምህርት አቅርቦትን ማስፋት፡፡

### 2.8.2 ኢመቴክን ለተሻለ የጤና አገልግሎት ማዋል

#### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

በርካታ ሃገሮች የህክምና አገልግሎት ዘርፋቸውን ዘመናዊ ለማድረግ ኢመቴክን ይጠቀማሉ፡፡ በጤናው ዘርፍ ኢመቴክን በመጠቀም የሚሰጡ አገልግሎቶች የርቀት ህክምናን፣ የጤና ዘርፍ ሥራ አመራርን፣ የጤና ኢንፎርሜሽን ማዕከል፣ የጤና ትምህርት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ፡፡ የጤና አገልግሎት አቅርቦትን ለመደገፍ

ኢመቴክን መጠቀም በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አብዛኛው ሕዝብ በገጠር አካባቢዎች ለሚኖር አገሮች እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም መንግሥት ኢመቴክን ለተሻለ የጤና አገልግሎት ለማዋል የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች በመጠቀም በመላው አገሪቱ በኢመቴክ የታገዘ የጤና አገልግሎትን ለማዳረስ ይሰራል፡፡

## 2/ ዓላማ

ኢመቴክን በመጠቀም የጤና አገልግሎትን ሽፋን ማሻሻል፣ ማስፋፋትና ዘመናዊ ማድረግ፡፡

## 3/ ግቦች

ኢመቴክን ለተሻለ የጤና አገልግሎት ማዋል የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና መሠረታዊ የጤና አጠባበቅን ለማስተማር የሚያስችል ኢንፎርሜሽን በኢንተርኔት በመጠቀም ለሕዝቡ በማዳረስ፣ በመከላከል ላይ የተመሰረተውን የአገሪቱ የጤና ፖሊሲና ስትርቴጂ መደገፍ፤

ለ/ በኢመቴክ የተደገፈ የጤና የኢንፎርሜሽን ማዕከል ማቋቋምና በመላው አገሪቱ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ ጥራትና ሽፋን ማሻሻል ዓላማ ባደረገ መልኩ ኢንፎርሜሽን ማሠራጨት፤

ሐ/ ስለ በሽታዎችና መድሃኒቶቻቸው ለጤና ባለሙያዎች ወቅታዊ ኢንፎርሜሽን ለመስጠት የሚያስችል የጤና ኢንፎርሜሽን መረብ ፕሮግራም ማቋቋም፤

መ/ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ ሆስፒታሎችን፣ የጤና ምርምር ተቋማትንና የጤና ማዕከላትን እርስ በእርስ በኢንፎርሜሽን መረብ ማስተሳሰር፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

ኢመቴክን ለተሻለ የጤና አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ አገራዊ የጤና አጠባበቅ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ማልማትና መተግበር፤

ለ/ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የጤና ተቋሞችና የህክምና ባለሙያዎች ስለ ጤንነት፣ መድሃኒት፣ ስለበሽታ ስርጭት ወ.ዘ.ተ. ወቅታዊ ኢንፎርሜሽን የሚያገኙበት የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋት፤

ሐ/ ኢመቴክን በመጠቀም በአገሪቱ የሚገኙ የህክምና አግልግሎቶችን አስተዳደር ማሻሻልና ዘመናዊ ማድረግ፤

መ/ በአገሪቱ ውስጥ የርቀት ህክምና በማስፋፋት የተሻለ የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኝበትን መንገድ መፍጠር፤

ሠ/ የበሽታ ስርጭትን ለመግታትና ለመቆጣጠር ኢመቴክን በመጠቀም የህክምና መልዕክቶችን ማስተላለፍ፤

ረ/ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ አፕሊኬሽኖችን በማጐልበት ወጪ ቆጣቢ የጤና አገልግሎት በመላ አገሪቱ ማዳረስ፤

ሰ/ የርቀት ትምህርትን ጨምሮ በኢመቴክ የታገዙ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን ለጤና ባለሙያዎች መስጠት፡፡

### 2.8.3 ኢመቴክን ለዘመናዊ የግብርና ዘርፍ ማዋል

#### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ከ80 በመቶ የማያንስ የአገሪቱ የገጠር አካባቢዎች የሚኖር ሕዝብ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራ ሲሆን አብዛኛው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢም የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የግብርናውን ዘርፍ ዘመናዊ ለማድረግ ኢመቴክ ሊኖረው የሚችለውን ሚና በመገንዘብ መንግሥት የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

#### 2/ ዓላማ

ኢመቴክን በዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራ፣ በክትትልና በኢንፎርሜሽን ልውውጥ ሂደት በመጠቀም የግብርና ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል፡፡

#### 3/ ግቦች

ኢመቴክን ለዘመናዊ የግብርና ዘርፍ ማዋል የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ ኢመቴክን በመጠቀም የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ማሻሻል፤

ለ/ የኢመቴክ አገልግሎትን በምርት ሂደትና ግብይት ወቅት በመጠቀም የግብርና ውጤቶች በዓለም ደረጃ በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መደገፍ፤

ሐ/ የእርሻ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚያስችል አገር አቀፍ የመልክዓ ምድራዊ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት መመሥረትና ሥራ ላይ ማዋል፤ ወቅታዊነቱንም እንዲጠብቅ ማድረግ፤

መ/ በግብርና ልማት ኢመቴክን በመጠቀም ቀጣይ እና ፈጣን ዕድገትን ማረጋገጥ፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

ኢመቴክን ለዘመናዊ የግብርና ዘርፍ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የተቀናጀ የግብርና ልማት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት ማልማትና መተግበር፤

ለ/ ኢንፎርሜሽን ለመላ የአገሪቱ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ለማዳረስ የተዋሃደ እና የተቀናጀ የግብርና ኢንፎርሜሽን የሚሠራጭበትን ሥርዓት (የግብርና ኔት) መዘርጋት፤

ሐ/ ዘመናዊ የግብርና ግብይት ሥርዓትን በማስፋፋት በገጠር የመልቲሚዲያ ማዕከሎችና የኢንፎርሜሽን መዳረሻ ተርሚናሎች እንዲቋቋሙ በማድረግ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በኢመቴክ አማካኝነት ወቅታዊ ኢንፎርሜሽን እንዲያገኙ ማድረግ፤

መ/ የአገሪቱን የግብርና ምርት እሴት ለማሳደግ የግብርና ተኮር ኢንዱስትሪዎች ኢመቴክን እንዲጠቀሙ ማበረታታት፤

ሠ/ የአገሪቱን እምቅ የግብርና ሀብት የሚመለከት አገራዊ የግብርና መረጃ የዳታ ማዕከል ማቋቋም፤

ረ/ በፌዴራል፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ አካባቢያዊ የሜትሮሎጂ ዳታ እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ሰ/ የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶቻቸውን በኢንተርኔት አማካይነት እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ ማበረታታት፤

ሸ/ የእንስሳት ዕድገት መከታተያ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት በመዘርጋት የእንስሳትን የህይወት ዑደት ኢንፎርሜሽን አደራጅቶ በመያዝ የጅምላ ሻጮች እና የችርቻሮ ደንበኞች ስለ እንስሳቱ ደህንነት እና የጤና ሁኔታ አስተማማኝ ኢንፎርሜሽን እንዲኖራቸው ማስቻል፤

ቀ/ ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮች፣ ለመስክ ሠራተኞችና ለሌሎች የገጠር ነዋሪዎች መሠረታዊ የኮምፒውተር ክህሎትን የሚያስጨብጡ የማህበረሰብ ኢንፎርሜሽን ማዕከሎችን ማቋቋም፡፡

## 2.9 የኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

የኢኮኖሚ ልማት በአጠቃላይና የኢመቴክ ልማት በተለይ በወሳኝነት የግሉን ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉ ዘርፍ በኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ ፈጣን ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ ግለሰቦችና አነስተኛ የንግድ ተቋማት በዘርፉ አገልግሎቶችን እየሰጡና የሥራ ዕድልም እየከፈቱ ይገኛል፡፡

የግሉ ዘርፍ ሀገሪቱ በኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት የምታደርገውን ጥረት በማፋጠን ረገድ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት በመገንዘብ መንግሥት የግሉን ዘርፍ የኢንዱስትሪ የልማት እንቅፋቶች ለማስወገድ የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2/ ዓላማ

ብቃት ያለውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የግሉ ዘርፍ የኢመቴክ ኢንዱስትሪ እንዲለማ ድጋፍ ማድረግ፡፡

### 3/ ግቦች

የኢመቴክ ኢንዱስትሪና የግሉ ዘርፍ ልማት ተሳትፎ ማሳደግ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ በኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት መስፋፋትና መጠናከር የግሉ ዘርፍ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፤

ለ/ ለኢመቴክ ልማት የሀገር ውስጥና የውጭ ቀጥተኛ የኢንቨስትመንትን ማበረታታት፤

ሐ/ የግሉን ዘርፍ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል አቅሙን ማጎልበት፤

መ/ የግሉ ዘርፍ የኢመቴክ አገልግሎቶችን በገጠር አካባቢዎች እንዲሰጥና እንዲያስፋፉ ማበረታታት፤

ሠ/ በአነስተኛ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ኢመቴክን ለሥራ ዕድል ፈጠራና ልማት እንዲጠቀሙ ማበረታታት፤

ረ/ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ የኤሌክትሮኒክ ውጤቶችን የሚያመርቱ ተቋማትን መደገፍ፡፡

### 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ ኢንዱስትሪና የግሉን ዘርፍ ልማት ተሳትፎ ለማሳደግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የሀገር ውስጥና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎች እንዲሁም ተቋማዊ አደረጃጀቶችን መዘርጋት፤

ለ/ የግሉ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኢመቴክ ኢንዱስትሪና አገልግሎትን ማደራጀት እንዲችል በጥናት ላይ የተመሰረተ ልዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

ሐ/ ኢመቴክን እንደ ልማት መሣሪያ ለመጠቀም በሚደረገው ርብርብ የግሉ ዘርፍ ድርሻውን እንዲወጣ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፤

ሐ/ የግሉ ዘርፍ የኢመቴክ አገልግሎቶችን ለገጠር አካባቢዎች እንዲያቀርብ የተለየ ማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤

መ/ የኢመቴክ የሥራ ዕድል ፈጠራ ማስፋፊያ ማዕከላት ማቋቋም፤

ሠ/ የኢመቴክ ፓርኮች ልማትን ማስፋፋትና ማጠናከር፤

ረ/ የኢመቴክ ኢንዱስትሪ ኢንፎርሜሽን ሥርዓት በማልማት በምርቱ ላይ፣ በሥራ ቅጥር እና በንግድ እንደዚሁም በኢንቨስትመንት እና ሌሎች ማበረታቻዎች ላይ ዳታ በማደራጀት የዘርፉን ነባራዊ ሁኔታ እና የወደፊት አቅጣጫ አጉልቶ ማሳየት፣

ሰ/ ዘርፉን ለማሳደግ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የልምድና የንግድ ትስስርን ሊያበረታቱ የሚችሉ ኤግዚቢሽኖችና ወርክሾፖች እንዲዘጋጁ ማድረግ፡፡

## 2.10 የኮምፒዩተር እና ተያያዥ አገልግሎቶች ልማት ማሳደግ

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

የተቀናጀ ሀገራዊ የሶፍትዌር ሥርዓት በመዘርጋት የኢመቴክ አጠቃቀምን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ እና ቀጣይነቱንም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሶፍትዌሮች፣ አገልግሎቶች እና የኢንፎርሜሽን ይዘቶችን ወደ አገር ውስጥ ቋንቋ መለወጥና ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማስማማት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ የሶፍትዌር ምርቶችና እና ተያያዥ አገልግሎቶች ኢንዱስትሪው የአገሪቱን ኢኮኖሚ ዘመናዊ ለማድረግ፣ የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት እና የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት ያለው እድል ከፍተኛ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ኢትዮጵያ የዘርፉን ውጤቶች ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል አቅም ይኖራታል፡፡

በአገር ውስጥ ጠንካራ የሶፍትዌር ምርቶች እና የኮምፒዩተር አገልግሎት ኢንዱስትሪ እንዲኖር ለማድረግ የአቅም ግንባታ፣ የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓትን ማጐልበት፣ ለንግድ ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ፣ የፋይናንስ ምንጮችን ማመቻቸት፣ ተገቢ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣ የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓት መዘርጋትና የአገር ውስጥ ፍላጐት ማሳደግን የሚያካትቱ ሥራዎችን መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የኮምፒውተርና ተያያዥ አገልግሎቶችን ለማሳደግ መንግሥት የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2/ ዓላማ

ጠንካራ ብሔራዊ የሶፍትዌር ኢንዱስትሪ በመፍጠር ኢመቴክ ለኮምፒውተርና ተያያዥ አገልግሎቶች አጠቃቀም ዕድገት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማጐልበት፡፡

## 3/ ግቦች

የኮምፒውተርና ተያያዥ አገልግሎቶች ልማት ማሳደግ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ የኮምፒውተር ሶፍትዌር እና አገልግሎቶችን በማልማት ሥራ ላይ ማዋል፤ በተለይም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ለ/ በኮምፒውተር ሶፍትዌር እና አገልግሎቶች ልማት ላይ የአገር ውስጥ እና የውጪ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፤

ሐ/ በአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊ እና ተወዳዳሪ የሆኑ የኮምፒውተር ሶፍትዌር እና አገልግሎቶች እንዲኖሩ ማድረግ፣

መ/ የኮምፒውተር ሶፍትዌር እና አገልግሎቶች ዘርፍ ወደ ውጪ የሚላኩ ሀገራዊ አፕሊኬሽኖች፣ ሶፍትዌር እና አገልግሎቶች ማምረት እንዲችል ማድረግ።

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኮሚፒውተርና ተያያዥ አገልግሎቶች ልማት ለማሳደግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ በኢመቴክ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰሩ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሶፍትዌር አምራቾች የማበረታቻ ሥርዓት በመዘርጋት ዘርፉን ማሳደግ፤

ለ/ ለኢንቨስትመንት የሚውል የፋይናንስ ምንጭ እንዲኖር በማመቻቸት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች በመደራጀት ማበረታቻ እንዲያገኙ እና በጋራ ጥምረት በዘርፉ እንዲሰማሩ መደገፍ፤

ሐ/ በሞባይል ዘርፍ ያሉ ኩባንያዎች ለሞባይል አፕሊኬሽን ሶፍትዌር አምራቾች ቤተ ሙከራዎችን በማደራጀት፣በማወዳደር እና የተግባር ልምምድ በመስጠት ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት፤

መ/ የሰርቲፊኬሽን እና የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት መዘርጋት፤

ሠ/ የሶፍትዌር ዕውቀትን በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት እና በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፤

ረ/ በዘርፉ የመንግስት ግዢ ፍላጐት እና የግሉ ዘርፍ ምርት የሚተሳሰርበትን ሁኔታ መፍጠር፤

ሰ/ የሶፍትዌር እና የሀርድዌር ምርትን ወደውጭ ለመላክ የሚያስችል ፕሮግራም ማመቻቸት፤

ሸ/ የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓቶችን መዘርጋት፡፡

## 2.11 የኢመቴክ የሥራ ሀሳብ እና ፈጠራን ማበረታታት

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

አነስተኛና ጥቃቅን የስራ ሃሳብ አፍላቂዎች እና የፈጠራ ባለቤቶች አዳዲስ ሀሳቦችን ወይም ቴክኒኮችን በመጠቀምና በማስተዋወቅ ውጤታማ መሆን በመላው ዓለም እየታየ ያለ ክስተት ነው፡፡ ከፊሎቹ ስኬታማ ባይሆኑም የተቀሩት በሂደት ከፍተኛ የሆነ የሥራ እድል በመፍጠርና በማስፋፋት ወደ ስኬት ማማ መድረስ ችለዋል፡፡ ጀማሪ መስራቾቹ ወጣት እና የኮሌጅ ተማሪዎች በመሆቸው ከዩኒቨርስቲ ምሩቃን ጋር በተያያዘ ያለውን የሥራ አጥነትን ለመቅረፍ ድርሻቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ስኬታማ የቴክኖሎጂ ጀማሪ ድርጅቶች በቢዝነስ ሞዴሉ ላይ ዓይነተኛ ተፅእኖ በማሳረፍ አዳዲስ በኢመቴክ የታገዙ ምርቶችና አገልግሎቶች ማስተዋወቅና መጠቀም ያስችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ደረጃ የሥራ ሀሳብና ፈጠራ ባለቤቶች ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማስፋፋት እና ሀገራዊ ዕድገቱን በመደገፍ ረገድ የሚኖራቸው ፈይዳ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም የኢመቴክ አዳዲስ የሥራ ሀሳብ አፍላቂዎች እና በፈጠራ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ለማሳደግ መንግሥት የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2/ ዓላማ

ለሥራ ሀሳብ እና ፈጠራ ባለቤቶች ተስማሚ የሆነ የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

### 3/ ግቦች

የኢመቴክ የሥራ ሀሳብ እና ፈጠራ ባለቤቶችን ማበረታታት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

ሀ/ ለጀማሪዎች ተስማሚ የሆነ ኢኮ-ሲስተም መፍጠር፤ እና

ለ/ የሥራ ሀሳብ አፍላቂዎች ዕድገት ማመቻቸት፡፡

### 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ የሥራ ሀሳብ እና ፈጠራ ባለቤቶችን ለማበረታታት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ በአገር ውስጥ የግሉን ዘርፍ ማበረታታት እና መደገፍ በተለይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልዩ የማበረታቻ ሥርዓት በመዘርጋት በኢመቴክ ኢንዱስትሪ ልማት እንዲሳተፉ ድጋፍ ማድረግ፤

ለ/ የኢመቴክ ፓርኮችን በማጎልበት ጀማሪ የኢመቴክ ድርጅቶች የሚፈልቁበትና የሚደራጁበት ማዕከል ማድረግ፤

ሐ/ ጀማሪ የኢመቴክ ድርጅቶችን የሚያበረታታ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት እና መደገፍ፤

መ/ የተለያዩ ኩነቶችን እና የጋራ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት እንዲሁም ውድድሮችን በማጎልበት ጀማሪ የኢመቴክ ድርጅቶችን እርስ በርሳቸው እና ከትላልቅ ኩባንያዎች ጋር ማስተሳሰር፤

ሠ/ በአነስተኛ የቴክኖሎጂ ሥራ ፈጠራ ላይ ለተሰማሩ የሥራ ፈጣሪዎች የማበረታቻ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ረ/ በሥራ ሀሳብ አፍላቂዎች የሚተዋወቁ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችንና ውጤቶችን ተያያዥ በሆኑ የመንግስት፣ የጤና፣ ትምህርት እና የገጠር ልማት ላይ መጠቀም፤

ሰ/ የኤሌክትሮኒክ ክፍያ አማራጭን በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውል ማመቻቸት፡፡

## 2.12 ኢመቴክ ለወጣቶች እና ለሴቶች

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

በመላው ዓለም ወጣቶችንና ሴቶችን ለማብቃት ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ አማራጭ በመስጠት፣ በማበረታታት፣ እንዲቀናጁ በማድረግ እና ድምፃቸው እንዲሰማ በማስቻል ረገድ ቴክኖሎጂው ድጋፍ አድርጎላቸዋል፡፡ ወጣቶች እና ሴቶች መልክአምድራዊ አቀማመጥ እና የድንበር አከላለል ሳያግዷቸው ለማሕበራዊ ጉዳዮች በጋራ ምላሽ እንዲሰጡ አስችሏቸዋል፡፡

ኢመቴክ ወጣቶችን እና ሴቶችን በማብቃት በማህበራዊ ዕድገትና በትምህርት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያነሳሳል፡፡ ወጣቶችና ሴቶችን በተለይ ለኢመቴክ የተሻለ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ በትምህርት፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት በንቃት ለማሳተፍና ራሳቸውንም በማሻሻል የሚታዩ የፆታ ክፍተቶችን ለመሙላት ያስችላል፡፡ ፍትሀዊ ተደራሽነት ያለው እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የኢመቴክ አገልግሎትን ወጣቶችና ሴቶች እንዲያገኙ ማድረግ የዲጂታል እና የማህበራዊ አካቶን እውን ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ኢመቴክን ለወጣቶች እና ሴቶች ለማድረስና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ መንግሥት የሚከተሉትን ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 2/ ዓላማ

በሁሉም ክልሎች የተለያዩ ዓይነት የኢመቴክ አገልግሎቶች ለወጣቶች እና ለሴቶች እንዲቀርቡ በማድረግ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

## 3/ ግቦች

የኢመቴክ አገልግሎቶችን ለወጣቶች እና ለሴቶች ማድረስ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

- ሀ/ በመላ ሀገሪቱ የጾታ ልዩነት በሌለበት ሁኔታ ወጣቶችንና ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ደህንነታቸው የተጠበቀ የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎቶችን ማቅረብ፤
- ለ/ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወጣቶችና ሴቶችን በማብቃት እና ያሉ ክፍተቶችን በመሙላት ረገድ የሚኖረውን ቁልፍ ሚና ማረጋገጥ፤
- ሐ/ በኢመቴክ ኢንዱስትሪ ወጣቶች እና ሴቶች የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

## 4/ ስትራቴጂዎች

የኢመቴክ አገልግሎቶችን ለወጣቶች እና ለሴቶች ለማዳረስ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

ሀ/ የትምህርት ሥርዓቱ ሁሉም ተማሪዎች የላቀ የኢመቴክ ክህሎት እንዲቀስሙ እኩል እድል የሚሰጥ መሆኑን በማረጋገጥ ሴቶች የኢመቴክ የሥራ እድል እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤

ለ/ ለትርፍ ያልተቋቋሙና በወጣቶችና በሴቶች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች በነፃ ወይም በመጠነኛ ዋጋ የኢመቴክ አገልግሎት እንዲያገኙ መደገፍ፤

ሐ/ የትምህርት ሥርዓቱ ኢመቴክን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በማሳወቅ ረገድ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል መስጠቱን ማረጋገጥ፤

መ/ ወጣት እና ሴት የቴክኖሎጂ እና አዳዲስ የሥራ ሀሳብ ፈጣሪዎችን ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እና ውድድሮች በማዘጋጀት ማበረታታት፤

ሠ/ ተገቢ እና ሕጋዊ የኮምፒዩተር ማዕቀፍ በማዘጋጀት የሳይበር ጥቃቶች እና ጉዳቶች በወጣቶች እና በሴቶች ላይ ተፅእኖ እንዳያደርሱ በአግባቡ መከላከል፡፡

## 2.13 የኢመቴክ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግርን መደገፍ

### 1/ አጠቃላይ ምልከታ

በአሁኑ ወቅት የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች በአጠቃላይና በተለይም ደግሞ በኢመቴክ ዘርፍ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ መንግሥት የምርምርና ልማት ኢንቨስትመንት ስራ ለኢመቴክ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዘርፍ ሳይንሳዊ እመርታ በማምጣት ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ያምናል፡፡ ስለዚህ የኢመቴክ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት በሀገሪቱ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በአጠቃላይና በኢመቴክ ልማት በተለይ የሚጫወተውን ጠቃሚ ሚና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መንግሥት የሚከተሉትን ተጨባጭ ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2/ ዓላማ

በኢመቴክ ዘርፍ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም በመገንባት ለአገሪቱ ዕድገትና ልማት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ መደገፍ እና አስተዋፅኦ ማድረግ፡፡

### 3/ ግቦች

በኢመቴክ ዘርፍ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም መገንባት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

- ሀ/ የኢመቴክ ምርምር መርሐ-ግብሮች አካባቢያዊ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኮሩ እና በአገራዊ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ እንዲሁም የባለሙያዎችን ክህሎት የሚያሳድጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ለ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ቤተሙከራዎች በመሳሰሉት የምርምር ማዕከላት ውስጥ ለሚደረጉ የኢመቴክ ምርምርምና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች ድጋፍ ማድረግ፤
- ሐ/ በሀገሪቱ የኢመቴክ የልህቀት ማዕከላትና በሌሎች አገራት ከሚገኙ ተመሳሳይ ማዕከላት ጋር ትብብርን በማሳደግ የዓለም ምርጥ ተሞክሮዎችና የምርምር አቅሞችን በሚገባ መጠቀም፤
- መ/ የኢመቴክ ባለሙያዎች በምርምር ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ማበረታታት፤

### 4/ ስትራቴጂዎች

በኢመቴክ ዘርፍ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም ለመገንባት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፤

- ሀ/ የኢመቴክ የምርምር ሥርፀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀት፤
- ለ/ ለሀርድዌርና ሶፍትዌር ልማት፣ ለመገናኛ፣ ለኢንፎርሜሽን መረብ፣ ወዘተ ተገቢ የምርምርና የልማት በጀት እንዲመደብ ማድረግ፤
- ሐ/ ፍላጐትን መሠረት ያደረገ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን በማበረታታት የቴክኖሎጂ ፈጠራ ደረጃን ማሳደግ፤
- መ/ መረጃን በቀላሉ ማግኘትና መጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ብዙ ተናጋሪ ላላቸው የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ቅድሚያ በመስጠት ለሆሄያት ሥርዓት፣ ለቋንቋ መግባቢያነት፣ ለኤሌክትሮኒክ መዝገበ ቃላትና የቃላት መፍቻ ላይ የሚደረጉ የምርምር ዘርፎችን ማበረታታት፤

ሠ/ በግልና በመንግሥት ተቋማት የተሠሩ የምርምር፣ ሥርፀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን በማስተሳሰር ከየዘርፉ የተገኙ ልምዶችና ምርጥ ተሞክሮዎችን መጋራት፤

ረ/ የግሉ ዘርፍ ለምርምር፣ ለሥርጸትና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች መዋዕለ ንዋይ መመደብ እንዲችል ልዩ ልዩ የማበረታቻ ሥርዓቶችን መዘርጋት፤

ሰ/ የምርምር ውጤት የሆኑ የኢመቴክ ዕድገትን የሚያሳዩ አዳዲስ ኢንፎርሜሽን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ።

## ምዕራፍ ሦስት
## የፖሊሲው የአፈጻጸም ማዕቀፍ

### 3.1 አጠቃላይ ምልከታ

የኢመቴክ ፖሊሲ ቀዳሚ ጉዳይ ፖሊሲውን ተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልገው የተቋማት አወቃቀር ነው። ኢመቴክ በባህሪው የተለያዩ ዘርፎችን የሚያቅፍ በመሆኑ ውጤታማ እንዲሆን የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍ፣ የማህበረሰብ ድርጅቶችንና የዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ተሳትፎ ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር መንግሥት ተፈላጊውን የሕግና የቁጥጥር ማዕቀፍ መፍጠር፣ የሕዝብን አቅም ማቀናጀት፣ አስፈላጊ ተቋማትን ማቋቋምና በሥራ ላይ ያሉትንም በማጠናከር ለፖሊሲው ትግበራ ስትራቴጂያዊ አመራር መስጠት ይጠበቅበታል። በየዘርፉ፣ በየክልሉና በየተቋማቱ መወሰድ የሚገባቸውን የኢመቴክ እርምጃዎችን ለማቀናጀት ስትራቴጂያዊ አመራር ያስፈልጋል። ይህም በዘርፎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በማዳበርና አቅምን በማሰባሰብ የሃብት ብክነትን ያስወግዳል።

ፖሊሲውን ሥራ ላይ ለማዋል መንግሥት የመሪነት ድርሻ የሚወስድ ሲሆን፣ የሚከተሉት የባለድርሻ አካላትም የሚጠበቅባቸውን የተለያዩ ቁልፍ ሚናዎችን ይጫወታሉ።

ሀ/ የተለያዩ መንግሥት ተቋማት

ለ/ የግሉ ዘርፍ

ሐ/ የትምህርትና የምርምር ተቋማት

መ/ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች

ሠ/ የመገናኛ ብዙሐን

ረ/ የልማት አጋሮች

ሰ/ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ...ወዘተ

የኢመቴክ ፖሊሲ ትግበራን በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ለማመቻቸትና ዘርፈ-ተኮር የሆኑ የኢመቴክ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡ የግሉ ዘርፍም በዚሁ እንቅስቃሴ ላይ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ያበረታታል፡፡

## 3.2 የተቋማት አወቃቀር

የኢመቴክ ዕድገትን ለመደገፍና ለማመቻቸት ተቋማዊ ብቃት አለመኖሩን በመገንዘብ መንግሥት ጠንካራ የኢመቴክ ዘርፍ ልማት እንዲኖር አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ የማዕዘን ድንጋዮች ማስቀመጥ ጀምሯል፡፡ እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ ምክንያት የሆነው በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የኢመቴክ ፈጣን የኢንዱስትሪ ዕድገትና በኢትዮጵያም የሚታየው ተመሳሳይ ሁኔታ ነው፡፡ እስከአሁን ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል ከዚህ በፊት በቀድሞው የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ፣ በቀድሞው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ እና በቀድሞው የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ለመገናኛው ዘርፍ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በማቀናጀት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን ማቋቋም አንዱ ነው፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኢመቴክ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን የመንደፍና አፈጻጸማቸውን የማስተባበር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መሠረታዊ ግብ ለኢመቴክ ልማትና ለውጤታማ አተገባበሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለብሔራዊ የልማት ሂደት የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂን ለሃገሪቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና መልካም አስተዳደር አስተዋጽኦ በሚያደርግ መልክ መጠቀም ነው፡፡ የኢመቴክን ልማትና አፈጻጸም የሚደግፉና የሚያመቻቹ ሌሎች ቁልፍ ሚና ካላቸው ባለድርሻ አካላት ውስጥ የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ባለስልጣንና የትምህርት ተቋማት የኢመቴክ ክፍሎች ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም የኢመቴክ ፖሊሲ አፈጻጸምን ለመደገፍ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡

ሀ/ ከምሁራን፣ ከባለሙያዎችና ከማህበረሰብ ድርጅቶች የተውጣጡ አባላት የሚኖሩት ብሔራዊ የኢመቴክ አማካሪ አካል ማቋቋም፣

ለ/ በኢመቴክ መሠረታዊ ልማትና ፖሊሲ አፈፃፀም ዙሪያ ብሔራዊ ኃላፊነት የተሰጣቸው መንግሥታዊ ተቋማትን የሚያስተባብርና የሚከታተል አካል እንዲቋቋም ማድረግ፤

ሐ/ በቂ እና ዘላቂነት ያለው አቅም በሁሉም የመንግስት ደረጃዎች እና በተለያዩ ዘርፎች እንዲገነባ በማድረግ ብሔራዊ የኢመቴክ መርሐ-ግብርን እና ፕሮጀክትን ተግባራዊ ማድረግ፡፡

መ/ ለብሔራዊ የኢመቴክ ልማት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ግልጽ የአጋርነት አሰራር ስርዓት ማስቀመጥ፤

ሠ/ የኢመቴክ መርሐ-ግብሮችና ፕሮጀክቶች ከብሔራዊ የኢመቴክ ልማት ዕቅድና መርሐ-ግብሮች ጋር ማቀናጀት፤

እንደአስፈላጊነቱ መንግሥት ለፖሊሲው አፈጻጸም በሚያመች ሁኔታ አዳዲስ ተቋማትን መፍጠር ወይም ያሉትን ማሻሻል ይችላል፡፡ የፖሊሲው የተለያዩ ክፍሎች ከሀገራዊ የልማት ቀዳሚ አጀንዳዎችና በዓለም አቀፍ የኢመቴክ ዘርፍ በሚደረጉ ለውጦች አንፃር በየጊዜው መከለስ ይኖርበታል፡፡

## 3.3 ክትትልና ግምገማ

የኢመቴክ የልማትና አፈጻጸም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንደዚሁም ዕቅዶችና መርሃግብሮች በሚገባ መቀናጀታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስልቶች ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፖሊሲው አፈጻጸም ቅንጅት፣ ቁጥጥርና ግምገማ በተመለከተ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፖሊሲው አፈጻጸም በሚፈለገው መንገድና አቅጣጫ መሄዱን በየጊዜው ቁጥጥርና ግምገማ በማድረግ ለማረጋገጥ እንዲቻል የመከታተያ መንገዶች የሚቀይስ ተቋማዊ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፡፡ ይህም የፖሊሲ ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች

መሳካታቸውንና ወቅታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እንደዚሁም እንደአስፈላጊነቱ የፖሊሲ ክለሳ መደረጉን ለማረጋገጥ ያስችላል።

የኢመቴክ ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚደረገው የማስተባር፣ የክትትልና ግምገማ ሥራ የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል።

ሀ/ የብሔራዊ የኢመቴክ ፖሊሲ፣ ፕላን፣ መርሃግብርና ስትራቴጂዎች ማመቻቸትና ማስተባበር፤

ለ/ በኢመቴክ ዕቅድና መርሐ-ግብር ቀረፃ ወቅት የሀብት ብክነትና አላስፈላጊ የሥራ ድግግሞሽ አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ/ የክንውን መለኪያዎችን እና ኢላማዎችን በማውጣት ውጤታማነቱን መለካት፤

መ/ ለብሔራዊ እና ዘርፍ-ተኮር መርሐ-ግብሮችና ፕሮጀክቶች ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው የፕሮጀክት አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ደረጃ ማውጣት፤

ሠ/ በመላ አገሪቱ ተደራሽ የሆነ የሀሳብ ማሰባሰብያ ድረገጽ እንዲኖር በማድረግ ተጠቃሚዎች በፍቃደኝነት ስለ ስትራቴጂው ትግበራ፣ የብሮድባንድ ፍጥነት፣ የአገልግሎት ጥራት እና መቆራረጥ ሁኔታ፣ ወ.ዘ.ተ. ጋር በተያያዘ ሀሳብ እንዲሰጡ ማድረግ፤

ረ/ ለተሻለ አሠራር በክልልና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል አጋርነትና ትብብርን ማጠናከር፤

ሰ/ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢመቴክን ልማት እንደዘርፍ ለማሳደግ በትጋት መሥራት፤

ሸ/ ለኢትዮጵያ ፈጣን የኢመቴክ ዕድገት ተገቢ በጀት እንዲመደብ በማድረግ እና ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ የፋይናንስ አቅምን በማሳደግ ብቁ እና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠርና ሥራ ላይ ማቆየት።

## 3.4 የወደፊት አቅጣጫ፣ ብሔራዊ የኢመቴክ መሪ ዕቅድ

ለፖሊሲው ተግባራዊነት ስትራቴጂያዊ ማዕቀፍ ያለው የብሔራዊ የኢመቴክ ማስተር ፕላን ማዘጋጀትና ለአፈጻጸሙ አስፈላጊውን ግብአት ማዘጋጀትን ይጠይቃል። ማስተር

ፕላኑ ለፖሊሲው የአፈጻጸም ክንውን ክትትልና ግምገማ መለኪያዎች፣ መነሻዎች፣ ግቦችና የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ኃላፊነቶችን የሚያስቀምጥ ይሆናል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በብሔራዊ ማስተር ፕላኑ የተቀመጡ የግቦችና ስትራቴጂዎች ማዕቀፍ ውስጥ የራሳቸውን ተጨባጭ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲቀርጹ ይደረጋል፡፡ የብሔራዊና የዘርፉ ዕቅዶችና መርሃግብሮች ለአፈጻጸሙ መሪነት በተግባር ዕቅዶች ይደገፋሉ፡፡

በፌዴራልና በክልል ደረጃ የኢመቴክ ፖሊሲ አፈጻጸምን ለማመቻቸት እንዲሁም የኢመቴክ ዘርፍ-ተኮር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና መርሃግብሮች ለማዘጋጀት በመንግሥታዊ ተቋማት አግባብ ያላቸው መዋቅሮች ይዘረጋሉ፡፡ የግሉ ዘርፍም የመንግሥት ተቋማትን ተሞክሮ መከተል እንዲችል ማበረታቻ ይደረጋል፡፡

የኢመቴክ የመጨረሻው ግብ በውጤታማ የኢመቴክ አጠቃቀም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ዘርፎችና በሁሉም የዜጐች የሕይወት መስኮች ትርጉም ያለው እድገትና የኑሮ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡